ፍኖተ

# ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት የካቲት 23 ቀን 2005 ዓ.ም. ቁጥር 66

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

# የፍኖተ ነፃነት የገቢ ማሰባሰቢያ ዘመቻ አበረታች ውጤት እያስገኘ ነው

በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ኤዲቶሪያል ቦርድ ስር የምትታተመው ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ህትመት ለማስቀጠል የተጀመረው ዘመቻ ከህዝቡ ጥሩ ምላሽ እያገኘ መሆኑን ኤዲቶሪያል ቦርዱ ገለፀ፡፡ ዘመቻውእንዲሳካቅስቀሳናትብብርበማድረግ ላይ የሚገኙ አካላትንም አስመስግኗል፡፡

ኤዲቶሪያል ቦርዱ ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደገለፀው የገቢ ማሳሰቢያ ዘመቻውን በሀገር ውስጥ ለማስተዋወቅ በተደረገው ጥረት በሸገር ኤፍ.ኤም እና በጋዜጦች ማስታወቂያ ተሰርቷል፡፡ በተለያዩ ሚዲያዎችም በዜና እና በቃለ መጠይቅ መልክ ለዘመቻው ሽፋን መስጠቱንም ጨምሮ አብራርቷል፡፡

“በውጪ ሀገር በተለይም በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ የሚገኙ ሬዲዮዎች እና ፖልቶክ ሩሞች ለገቢ ማሰባሰቢያ ዘመቻው ትኩረት ሰጥው በመቀስቀስ ላይ ይገኛሉ፣ በተለይም ኢሳት ሬዲዮ በዜና እና በቃለመጠይቅ ለዘመቻው ሽፋን ከመስጠቱም በተጨማሪ ያለአንዳንች ክፍያ ለገቢ ማሰባሰቢው የተሰራውን የቅስቀሳ ማስታወቂያ በማስተላለፍ ሀገራዊ ግዴታውን ተወጥቷል” ብሏል፡፡ “የቃሌ ኢትዮጵያ ፓልቶክ ሩምም በዘመቻው ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እያደረገ ያለው ቅስቀሳ ያስመሰገነዋል፡፡” ያለው እዲቶሪያል ቦርዱ በርካታ ተሳታፊ ያለው ኢትዮጵያን ከረንት አፌርስም የቃሌ ኢትዮጵያን መንገድ በመከተል ትብብር እንደሚያደርግ እምነቱን ገልጧል፡፡

እስካሁን እየተሰበሰበ ያለው ገቢ በእቅድ በተያዘው መሰረት እየተከናወነ መሆኑን የገለፀው የቦርዱ የገቢ ማሰባሰቢያ ዘመቻው ከሀገር ውስጥና ከውጪ ሀገር አስገራሚ ምላሽ እያገኘ ነሆቡን በመግለፅ ዘመቻው ከ3 ወር በላይ ስለሚቀረው ሁሉም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቋል፡፡

## 33ቱ ፓርቲዎች ዛሬ የመግባቢያ ስምምነት ይፈራረማሉ

6

## የኢህዴድ አመራሮች ከአባ ገዳዎች ላይ ከ400 ሺ ብር በላይ መመዝበራቸው ተገለጸ

2

## ነፃ ማተሚያ መሣሪያ ለነፃ ፕሬስ!

4

ዶ/ር ኃይሉ አርአያ

## በሙስሊሙ ሕብረተሰብ ላይ እየደረሰያለው የሰብአዊ መብት ጥሰት ያሳስበናል

2

## ርእሰ አንቀጽ

# በሙስሊሙ ሕብረተሰብ ላይ እየደረሰያለው የሰብአዊ መብት ጥሰት ያሳስበናል

አሁን በስራ ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ህገመንግስት፣ መንግስት በሃማኖት የውስጥ ጉዳይ እንዳይገባ ቢከለክልም፣ የኢህአዴግ መንግስት ግን እንዳሻው በሁሉም ሃይማኖቶች ተቋማት የውስጥ ጉዳይ ያለከልካይ ገብቶ እያቦካ ይገኛል፡፡

የዕምነት ነፃነት አምልኮን በነፃነት ማካሄድን፣ ዕምነትን ማስፋፋትንና የእምነት ተቋማትን በነፃነት ማስተዳደርን የሚያካትት ነው፤ አንዱ ሃይማኖታዊ አላባ ተከብሮ ሌላኛው አላባ እየተጣሰ የሃይማኖት ነፃነት ተከብሯል ቢባል ከመንግስት ውጪ ማንንም የሚያሳምን አይሆንም፡፡

ኢህአዴግ አምባገነናዊ ስርአቱን ለማስቀጠል ሲል የዕምነት ተቋማትንና መሪዎቹን በቁጥጥሩ ስር ሲያደረግ ኖሯል፡፡ ይህ አንባገነናዊ ድርጊት በሙስሊም ኢትዮጵያውያን ላይም ተግባራዊ በመደረጉ ምዕመናኑ የመንግስትን ድርጊት በመቃወም ከአንድ አመት ለበለጠ ጊዜ ጠንካራ ሰላማዊ ትግል አድርገዋል፤ እያደረጉም ይገኛሉ፡፡

መንግስት አለመግባባቱን ለመፍታት የቀረቡለትን ሶስት ጥያቄዎች ከመፍታት ይልቅ በማን አለብኝነት የትግሉን ግንባር ቀደም መሪዎች ከማሰር ባለፈ በምዕመናኑ ላይ ኢሰብአዊ ጥቃቶችን ማድረሱ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

ለኢህአዴግ ህገመንግስትን የመጣስ ድርጊት አዲስ ባህሪው ባይሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ በሙስሊም ኢትዮጵያውያን ላይ እያደረሰ ያለው የመብት ረገጣውን ማጠናከሩ ያሳስበናል፡፡ ለፍኖተ ነፃነት ምስክርነታቸውን የሰጡ ሰለባዎች እንዳረጋገጡት ባለፉት ሳምንታት ቤታቸው ያለፍርድ ቤት ማዘዣ በሌሊት ተበርብሯል፣ እንግልት ተፈፅሞባቸዋል እንዲሁም የንብረት ዝርፊያም ተፈፅሞባቸዋል፡፡ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሱ ሌሎች ታአማኒ መረጃዎች እንደሚያመላክቱትም የፍርድ ቤት ብርበራ ወጣባቸው የተባሉትም ግለሰቦች ስማቸው የተሞላው በፍርድ ቤት ሳይሆን ብርበራውን ባካሄዱትፖሊሶች ነው፡፡ ይህ የመንግስት ሀይሎች ድርጊት ችግሩን ከማባባስ ባለፈ የሚያመጣው መፍትሄት አይኖርም ብለን እናምናለን፡፡

መንግስት የዜጎችን ደህንነት የማስጠበቅ ግዴታ አለበት፤ ስለሆነም ይህ አይነቱ ህገወጥና ሀላፊነት የጎደለው ድርጊት እንዳይቀጥል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ መንግስት የተበደሉ ዜጎችን ቅሬታ በማጣራትም በህገወጥ ድርጊት በፈፀሙ ሃይሎቹ ላይ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ ብርበራው የተካሄደባቸው ግለሰቦች በተጨባጭ ወንጀል ተጠርጥረውም ከሆነ ብርበራው በቀን መካሄድ ነበረበት ብለን እናምናለን፡፡ በጠራራ ሌሊት የግለሰቦችን ቤት መበርበሩ ህዝብን ከማሸበር ያለፈ ውጤት የለውም፡፡

ሆኖም መንግስትም ሆነ ብርበራውን ያካሄደው ፖሊስ በጉዳዩ ላይ ምላሽ ለመስጠት አለመፈለጋቸው ተግባሩ እንደተለመደው ፖለቲካዊ አንድምታ እንዳለው ያስረዳል፡፡ ይህ የሰብአዊ መብት ጥሰት ገለልተኛ ነን በሚሉት የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽንና የእንባ ጠባቂ ተቋም መጣራትና መጋለጥም ነበረባቸው፡፡

የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላነሷቸው ግልፅ የመብት ጥያቄዎች ብልሀት የተሞላበት ምላሽ መስጠት ያቃተው የኢህአዴግ መንግስት እየወሰዳቸው ያሉት ኢህገመንግስታዊ እርምጃዎች ያሳስቡናል፤ በሙስሊሙ ሕብረተሰባ ላይ እየደረሰያለው የሰብአዊ መብት ጥሰት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ለመድረሱ ከመንግስት ሌላ ተጠያቂ የሚደረግ አካል አይኖርም፡፡

# የኦህዴድ አመራሮች ከአባ ገዳዎች ላይ ከ400 ሺ ብር በላይ መመዝበራቸው ተገለጸ

በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን አመራሮች በየ6 ዓመቱ ለአባገዳው መሪ ከማህበረሰቡ የሚሰበሰበውን ስጦታ እኛ እንሰበስባለን በማለት የሰበሰቡትን 400 ሺህ ብር ለግል ጥቅማቸው ማዋላቸው ከዞኑ ለፍኖተ ነፃነት የደረሱ ጥቆማዎች አመለከቱ፡፡

የዞኑ አመራሮች ለአባገዳው ከተሰጠው ስጦታ ከሰበሰቡት ገንዘብ በተጨማሪ ከህዝቡ የተበረከተውን የበግ ስጦታም ለግል ጥቅማቸው አውለዋል ያሉት የዞኑ ምንጮች ድርጊቱ በዞኑ የኦህዴድ አመራሮችና በአባገዳዎች መካከል ከፍተኛ አለመግባባት በመፍጠር ላይ ይገኛል ፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎች ከፍተኛ ቅሬታ እንደተሰማቸው በመግለጽ የዞኑ አመራሮች ታሪካዊውን የአባ ገዳ ሥርዓት ማናናቃቸውን ያሳያል ሲሉ በተለይ ለፍኖተ ነፃነት ገልጸዋል፡፡ ጉዳዩን በተመለከተ ከቦረና ዞን አመራሮች ጋር ለማጣራት ተደጋጋሚ ጥረት ብናደርግም አልተሳካም፡፡ የክልሉን ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ አቶ አብርሃምንም ለማናገር ያደረግነው ጥረት ስልካቸውን ባለማንሳታቸው አልተሳካም፡፡





# የአንድነትን ጽህፈት ቤት ለመዝጋት ደረገውን ሙከራ የጎንደር ህዝብ አከሸፈ

በሰሜን ጎንደር ምዕራብ አርማጮ ወረዳ የሚገኘውን የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ጽ/ቤት የሰሜን ጎንደር ዞን የኢህአዴግ አመራሮች ለመዝጋት ያደረገው ሙከራ በአካባቢው ነዋሪዎችና በፓርቲው አባላት ጥረት እንደከሸፈ የወረዳው የፓርቲ አመራሮች ገለፁ፡፡

በተለይ የጎንደር ከተማ አስተዳደር የፀጥታ ኃላፊ አቶ ወርቁ ኃይለማርያም ምዕራብ አርማጮ ወረዳ ድረስ በመሄድ ቤታቸውን ለአንድነት ፓርቲ ያከራዩትን ግለሰብ በማስፈራራት ባለቤቱን እርምጃ ሊወስዱባቸው እንደተዘጋጁና ቤታቸውንም በአስቸኳይ እንዲያስለቅቁ ማስጠንቀቂያ በመስጠታቸው ባለቤቱ የወረዳውን አንድነት ፓርቲ አመራሮች እባካችሁ ታፔላውንም ንቀሉና ቤቴን ልቀቁልኝ እኔ መኖር እፈልጋለሁ ሲሉ በልቅሶ መማፀናቸው ታውቋል፡፡

የወረዳው የብአዴን/ኢህአዴግ ጽህፈት ቤት ሃላፊ አቶ አክሊሉ ወንድማገኝም በተደጋጋሚ ጽ/ቤቱ እንዲዘጋ በአካባቢው የአንድነት ፓርቲ አባላትንና አመራሮችን ለማስፈራራት ቢሞክሩም እንዳልተሳካ በማወቃቸው የጎንደር ከተማ አስተዳደር የፀጥታ ኃላፊ አቶ ወርቁ ኃይለማርያም ምዕራብ አርማጮ በመሄድ አካራዩን እንዳስፈራሩ ከስፍራው የፓርቲው አመራሮች ለፍኖተ ነፃነት ገልፀዋል፡፡

በተለይ የአካባቢው የአንድነት ፓርቲ አመራሮች እንደገለፁልን ከሆነ ምንም እንኳ አከራዩ ከውል ውጭ የፓርቲውን ማስታወቂያ(ታቴላ) ንቀሉና ቤቴን ልቀቁ እያሉ ቢያለቅሱም እሳቸውን አያስፈራሩ፤ ባለጉዳዮቹ እኛ ስለሆንን ከፈለጉ መጥተው ያናግሩን በማለት ምላሽሰጥተዋል፡፡ የወረዳው የአንድነት አመራሮች "ፓርቲያችን በአካባቢው ከፍተኛ ተቀባይነትን በማግኘቱ ኢህአዴግ ፈርቶ በእጅአዙር ጽ/ቤት ለማስለቀቅ አስቦ የተለያዩ ጫናዎችን ቢፈጥርም እኛ ግን ህግን ተከትለን ስራችንን እንቀጥላለን" ብለዋል፡፡

"የአካባቢው የመንግስት አመራሮች በግልፅ ህግ እየጣሱ፣ በእኛና በልጆቻችን ላይ ህገወጥ ድርጊት እየፈፀሙ እያየን ዝም አንልም" በማለት ለፍኖተ ነፃነት የተናገሩት የወረዳው ነዋሪዎች "ከዚህ በፊት እንዳከሸፍነው ሁሉ ከእንግዲህም በአካባቢያችን የተከፈተውን የአንድነት ፓርቲ ቢሮ እንዳይዘጋ የተቻለንን እናደርጋለን፤ ህዝቡን አስተባብረን እንታገላለን" ሲሉ ያነጋገርናቸው የወረዳው ነዋሪዎች ገልፀውልናል፡ ፡ ጨምረውም ፓርቲው በአካባቢው ሌሎችጽ/ቤቶችንእንዲከፍትየአካባቢው ህዝብ እየጠየቀ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በተለይ የምዕራብ አርማጮ ወረዳ የአንድነት ሰብሳቢ አቶ አንጋው ተገኝን የሰሜን ጎንደር ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ግዛት አብዩ እና የዞኑ የፀጥታ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ወርቁ ኃይለማርያም ጥር 18 ቀን 2005 ዓ.ም. ከቀኑ በ 8፡ ሰዓት ወረዳው ድረስ በመሄድ "ከእንግዲህ በኋላ የብአዴን/ኢህአዴግ አባል ካልሆንክ ወረዳውን መልቀቅ አለብህ አለበለዚያ እርምጃ እንወስድብሃለን በማለት ጠርተው እንዳስፈራሩኝ ህዝብ እንዲያውቅልኝ እፈልጋለሁ" ካለበኋላ "ከሌሎች አባሎቻችን ጋር ህግን ተከትለን እስከሰራን ድረስ እንደማልፈራ ነግሬያቸዋለሁ" ሲል አክሏል፡፡ አሁንም ድረስ ቤቴ ሳይቀር ማታ በፀጥታ ሃይሎች እየተከበበ ነፃነቴን ቢያሳጡኝም ከቆምኩለት ትክክለኛ እና ህጋዊ ዓላማ ወደኋላ አልልም ሲሉ ለፍኖተ ነፃነት ገልፀዋል፡፡

የጋዜጣው ዝግጅት ክፍልም ስለጉዳዩ የዞኑ ዋና አስተደዳሪ የሆኑትን አቶ ግዛት አብዩ እና የፀጥታ ዘርፍ ኃላፊ የሆኑትን አቶ ወርቁ ሃይለማርያምን ምላሽ እንዲሰጡን ተደጋጋሚ ጥረት ብናደርግም አልተሳካም፡፡



# ነፃ ማተሚያ መሣሪያ ለነፃ ፕሬስ!

ኃይሉ ኣርኣያ

ዴሞክራሲ በታላቅ ግርማ ሞገስ የሚጎርፍ፣ የሚተም ትልቅ ወንዝ፣ ትልቅ ዠማ ነው:: ትልቅነቱን፣ ጥንካሬውንና ግርማ ሞገሱን የሚያገኘው በትጋት ሳያቋርጡ ከሚመግቡት ገባር ወንዞቹ ነው:: ከእነዚህ ትጉና ንቁ ገባር ወንዞች ዋናዎቹ ነፃና ብቁ ፕሬስ፣ ጠንካራ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ነፃና ጠንካራ ሲቪክ ድርጅቶችና ንቁ ሕዝብ ናቸው:: እነዚህ የዴሞክራሲ ገባር ወንዞች ከሌሉ፣ ዴሞክራሲ የሚባል ዠማ የለም:: አለም ከተባለ ለይስሙላ ጭልጭል የሚል እንጂ እንደ ዠማ የሚተም፣ አይሆንም::

ኢህአዴግ ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ዠማ እንዲተም፣ እንዲጎርፍ አይፈልግም:: በሌላ በኩል ከዴሞክራሲው ዓለም ጋር እንዳያጣላውና ከጭንቅ ለመውጣት የሚያስፈልገውን የኢኮኖሚ ርዳታ እንዳያሳጣው ጨርሶ እንዲጠፋም አይፈልግም:: ስለዚህ የኢህአዴግ ስትራተጂ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ አለ ብሎ ለመከራከርና ለማስመሰል በሚያስችለው መጠን ለእይታ ያህል ጭልጭል እንዲል ማድረግ ነው:: የዚህ ስትራተጂ አንዱ ዋና ክፍል ደግሞ ገባር የተባሉ የዴሞክራሲ ወንዞችን ማዳከም ነው:: እነዚህ ገባር ወንዞችም ጨርሰው እንዲጠፉ አይፈለጉም:: ነፍስ ዘርተው፣ ተጠናክረው ዴሞክራሲን የማጠከር ሚና እንዲጫወቱ ግን ፈጽሞ አይፈለግም:: ሁሉም በአሳሪና አስፈሪ ሕጎች ተገድበወዋል:: የዴሞክራሲ ዠማ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ገባሮቹ መጠናከር አለባቸው:: ለዛሬ፣ በዚህ አጭር ጽሑፍ ከገባሮቹ በአንዱ፣ ማለትም ፣ በነፃ ፕሬስ ላይ አተኩራለሁ::

ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ነፃ ፕሬስ ከፍተኛ አደጋ ላይ ይገኛል:: በአሳሪና አስፈሪ የፕሬስ አዋጅ ተጠፍሯል:: ጋዜጠኞች ሰበብ አስባብ እየተፈለገ በየፍርድ ቤቱ እየተጎተቱ ነው:: ወደ እስርቤት እየተጣሉ ነው:: እየተሰደዱም ነው:: የጋዜጣ፣ የመጽሔት፣ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ዋጋ ሰማይ ጠቅሷል:: በሀገሪቱ ሕገመንግሥት ቀርቷል የተባለ ቅድመ ምርመራ(ሳንሱር) በብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ጓሮ በኩል በእጅ ኣዙር ተመልሶ እንዲመጣ እየተደረገ ነው:: ሌሎች በከተማው ያሉ ማተሚያ ቤቶችም ሳንጃ የተከለ ጠመንጃ ወድሮ የሚያስፈራራ ኃይል ያለባቸው ይመስል "የተቃዋሚ ጋዜጣን አናትምም" ብለዋል:: ሠርቶ የማትረፍና ሀብት የመፍጠር ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን እንዲሁም ሕዝብን የማገልገል ግዴታቸውን በፍርሀት ጨርቅ ገንዘው በየማተሚያ ቤታቸው ጓሮ ቀብረውታል:: የሕዝብ ንብረት የሆኑ፣ በሕዝብ ሀብት የሚተዳደሩ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ሃያ አራት ሰዓት በኢህአዴግ በሞኖፖል ተይዘዋል:: ሌሎችም የተለያየ ስም እየተሰጣቸው በአየር ላይ አለን የሚሉ ጣቢያዎች ልሳናቸው የበዛ

የጋዜጣ፣ የመጽሔት፣ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ዋጋ ሰማይ ጠቅሷል:: በሀገሪቱ ሕገመንግሥት ቀርቷል የተባለ ቅድመ ምርመራ(ሳንሱር) በብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ጓሮ በኩል በእጅ ኣዙር ተመልሶ እንዲመጣ እየተደረገ ነው:: ሌሎች በከተማው ያሉ ማተሚያ ቤቶችም ሳንጃ የተከለ ጠመንጃ ወድሮ የሚያስፈራራ ኃይል ያለባቸው ይመስል "የተቃዋሚ ጋዜጣን አናትምም" ብለዋል:: ሠርቶ የማትረፍና ሀብት የመፍጠር ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን እንዲሁም ሕዝብን የማገልገል ግዴታቸውን በፍርሀት ጨርቅ ገንዘው በየማተሚያ ቤታቸው ጓሮ ቀብረውታል::

ቢመስልም ከሞላ ጎደል ቋንቋቸው አንድ ነው:: ያ ቋንቋ ግን የእውነተኛ ነፃ ፕሬስ ቋንቋ አይደለም:: በዚህ ዓይነት የፕሬስ ሁኔታ በሀገራችን ዴሞክራሲ ሊኖር አይችልም::

በአሁኑ ጊዜ ግልጽ ሆኖ የወጣው ነገር የነፃ ፕሬስ የመኖርና ያለመኖር ዕድል ያለው በገዢ ፓርቲ እጅ ብቻ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ በመንግሥትም ሆነ በግል ማተሚያ ቤቶች እጅም ጭምር መሆኑ ነው:: በተጨማሪ እያደር ግልጽ እየሆነ የመጣው ሌላ ነገር ነፃ ማተሚያ ቤቶች በሌሉበት ነፃ ፕሬስ ሊኖር እንደማይችል ነው:: በዚህ ጊዜ ነው አንድነት የራሱ የሆነና ለመጀመሪያ ጊዜ በነፃነት የሚያትም መሣሪያ እንዲኖረው የወሰነው::

አንድነት በአሁኑ ጊዜ ማተሚያ መሣሪያውን ለመግዛት የገንዘብ አቅሙ የለውም:: ነፃ ፕሬስና ነፃ ማተሚያ ቤቶች በኢትዮጵያ እንዲያብቡ ከሚመኙ ወገኖች ድጋፍ ያስፈልገዋል:: ስለዚህ ማተሚያ መሣሪያውን ለመግዛት የሚያስችለውን ገንዘብ ለማግኘት የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዘመቻ ጀምሯል:: በዚህ ዘመቻም በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ላሉ ኢትዮጵያውያን የዕርዳታ ጥሪውን እያቀረበ ነው::

እዚህ ላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ አንድ ነገር አለ:: ይኸውም ይህ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዘመቻ የአንድ ድርጅት ፍላጎትን ብቻ ለማሳካት የሚካሄድ ነገር እንዳልሆነ ነው:: አዎ፣ ዘመቻው ላይ ላዩን ሲያዩት አንድነት የማተሚያ መሣሪያ ለመግዛትና ጋዜጣ ለማተም የሚያስችለውን ገንዘብ ለማሰባሰብ ነው:: ሰፋ ተደርጎ ከታየ ግን ጉዳዩ ከዚህ ርቆ ባለፈ ትርጉም አለው:: ነፃ ፕሬስን ለማዳን፣ ከዚያም አልፎ ዴሞክራሲን ለማጠናከር የሚደረግ ዘመቻ ነው:: ነፃ ፕሬስንና ዴሞክራሲን ማጠከር ደግሞ የሁሉም የዴሞክራሲ ኃይሎች የጋራ ሥራ ነው::

አንድነት የራሱ የሆነ ማተሚያ መሣሪያ ቢኖረው ከመንግሥትና ከግል ማተሚያ ቤቶች ጥገኝነት ነፃ የመውጣትና የህትመት ሥራውን የማስፋት አቅም ይሰጠዋል:: ፍኖተ ነፃነትን ብቻ ሳይሆን መጻሕፍትን፣ መጽሔቶችንና ሌሎች መረጃ የመስጫና የማስተማሪያ ህትመቶችን የማዘጋጀት አቅም ይሰጠዋል:: ይህ ደግሞ ሕዝብን በተለያየ መንገድ ለመድረስ ያስችለዋል:: ይህ ከዚህ በላይ የተገለጸው አቅም በአንድነት ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም:: በቅድሚያ የአንድነት መጠናከር ማለት የሌሎች የዴሞክራሲ ኃይሎችም መጠናከር ማለት ነው:: በሌላ በኩል የአንድነትን አቅም ሌሎች የዴሞክራሲ ኃይሎችም በተቻለ መጠን በተግባር የሚጋሩት ይሆናል::

በአንድነት የተጀመረው የገንዘብ ማሰባሰብ ዘመቻ ለአራት ወራት ያህል ይዘልቃል:: ዓላማውም በዚህ ጊዜ ውስጥ ቢያንስ አንድ ሚሊዮን ብር ለማሰባሰብ ነው:: ዘመቻው የተለያዩ ክንዋኔዎች ይኖሩታል:: ከእነዚህ ዋናዎቹ በጥሩ መልክ የተዘጋጁና ከ30ብር እስከ 1000 ብር ዋጋ ያላቸው ካርዶች ሽያጭ፥ የመጻሕፍት ሽያጭና በቴሌኮንፈረንስ የሚደረግ ገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ናቸው:: አንድነት የጀመረው ዓላማ የዴሞክራሲ ኃይሎች የጋራ ዓላማ ነው:: የሕዝቡ ዓላማ ነው::

ስለዚህ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር የምትኖሩና ነፃ ፕሬስ በሀገራችሁ እንዲኖር የምትመኙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዛችሁ አንድነት የተያያዘውን የገንዘብ ማሰባሰብ ዘመቻ እንዲሳካ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታደርጉ ጥሪዬን አቀርባለሁ::

የጋራ ዓላማችንን በጋራ ጥረት እንሳካ!





# ሙስሊም ወጣቶች ከደቡብ ወሎ እየተሰደዱ ነው

በደቡብ ወሎ ወረባቡ ወረዳ በኃይማኖት ሰበብ በርካታ ወጣቶች እየታሰሩ በመሆኑ ብዙዎች ከኢትዮጵያ እንዲሰደዱ እንደሆነ የጥቃቱ ሰለባ ወጣቶች በተለይ ለፍኖተ ነፃነት ገለፁ::

በተለይ ከሙስሊሙ የኃይማኖት ነፃነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ የአካባቢው የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ወጣቶች ያለምክንያት እየታሰሩ በዋስ እንደሚለቀቁም ምንጮቻችን ጠቁመዋል::

የመንግስትን እስርና እንግልት ሸሽተው ከሚሰደዱ ወጣቶች መካከል የወሎ ዩኒቨርስቲ ተመራቂ ተማሪም እንደሚገኝበት ተገለፀ ሲሆን ከሀገር ተሰደው የመን ከገቡት መካከል የወሎ ዩኒቨርስቲ 4ኛ ዓመት ተማሪ እና የአንድነት ፓርቲ አባል ወጣት አሊ ሰይድ የመን በሚገኙ አጋቾች ታግቶ እንደሚገኝ ምንጮቻችን በተለይ ለፍኖተ ነፃነት ገልፀዋል::

ሌላው ወጣት ከድር መሐመድ በወረባቡ በሚገኝ መስጂድ ለፀሎትና ስግደት ቢሄድም በመስጂዱ ውስጥ የኮሚቴው ተጠሪ እንደሆኑ የሚነገርላቸው ሼህ "እጅህን ስጥ" በሚል ተኩስ ከፍተውበት ጉዳት ሳይደርስበት እንዳመለጠም ተጠቁሟል:: በዚህም ምክንያት የወጣት ከድር መሐመድ እናትና አባት ታስረው በዋስ እንደተለቀቁ ከስፍራው የደረሰን መረጃ አመልክቷል::

ከዚህ ጋር በተያያዘ የአካባቢው የአንድነት ፓርቲ አባል ወጣት ሰለሞን ፀጋዬም ታስሮ በ 5,000 ብር ዋስ ተለቋል:: ይህን እስከዘገብንበት ሰዓት ድረስም በርካታ የአካባቢው ወጣቶች የተሰወሩ ሲሆን ከነዚህ መካከልም ወጣት ከካሊድ ተስፋዬ፣ ሙስጠፋ ዑመር፣ ሀቢብ ኢብራሂም፣ ቢላል አየለ፣ አብዱራህማን ማህሙድ፣ መሐመድ አብዶ፣ ከድር እንድሪስ፣በድሩ፣ አብዱልከሪም የት እንዳሉ አይታወቅም::

በጉዳዩ ዙሪያ ያነጋገርናቸው የወረዳው ፖሊስ ኢንስፔክተር መስፍን እኔ ታምሜ እቤት ተኝቻለሁ፣ ጉዳዩ ገና በምርመራ ላይ ያለ በመሆኑ ከእኔ ሌላ የሚተባበርህ ሰው ልሰጣችሁ አልችልም፤ ከፈለጋችሁ በሌላ ጊዜ በአካል መጥታችሁ ዝርዝር መረጃውን መውሰድ ትችላላችሁ ሲሉ ምላሽ ሰጥተውናል::

# አንድነት ፓርቲ የዞንና የወረዳ እንቅስቃሴውን እየፈተሸ ነው

አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ የዞንና የወረዳ ም/ቤቶችን እንቅስቃሴ እየገመገመ በማጠናከር እየሠራ መሆኑን ከፓርቲው ድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ያገኘነው መረጃ አመለከተ::

በመረጃው መሠረት የድርጅት ቋሚ ኮሚቴ የቀጠና አደረጃጀችን ወደ የአካባባው በመሰማራት የዞንና የወረዳዎችን እንቅስቃሴ እንዲገመግሙ አድርጓል:: ጠንካራ ም/ቤቶች የበለጠ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ሲደረግ ድክመት የታየባቸውና በተለያየ ምክንያት የአመራር አባላት መጓደል የተፈጠረባቸው ም/ቤቶች ተሟልተው እንዲቀጥሉ ተደርጓል::

ቋሚ ኮሚቴው እንደገለፀው በተለይ በሰሜን ቀጠና በደቡብ ቀጠና ጠንካራ ሥራዎች የተሰሩ ነው:: በአንዳንድ ዞንና ወረዳዎች ኢህአዴግ የየአካባቢውን አመራሮች በማሰር በማዋከብና በማስፈራራት እንቅስቃሴውን ለመግታት ቢሞክርም ትግሉ ቀጥሏል ያሉት ኮሚቴው አባላት ባለው የገንዘብ አቅም ውስንነት የሚፈልገውን ያህል የማደራጀት ሥራ እየተሰራ ነው ተብሎ አይታሰብም::›› ሲሉ አስረድተዋል::

ተመሳሳይ ሁኔታ ህዝብ ግንኙነት ባደረሰን ዘገባ ግንኙነት ጠንክሮ እየሠራ ነው:: ተብሎአል:: በዚሁ መሠረት ተከታታይነት ያላቸው በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ የውይይት መድረኮች እየተከናወኑ መሆናቸው ተገልጾአል::

# አድዋ በዓል በአንድነትና በመኢአድ ጽ/ቤት ሊከበር ነው

አድዋ በዓል በአንድነትና በመኢአድ ጽ/ቤት ዛሊከበር ነው የኢጣልያን ወራሪ ጦር በአድዋ ላይ የተደመሰሰበት 117ኛ ዓመት የድል በዓል በአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ እና በመላው ኢትዮጵያ አንነት ድርጅት /መኢአድ/ ጽ/ቤት በተለያየ ዝግጅት እንሚከበር ታወቀ ::

ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው የአድዋ በዓል የሚከበረው በአንድነት ጽ/ቤት የካቲት 23 ቀን 2005 ዓ.ም ከ3ሰዓት ጀምሮ ሲሆን በመአኢአድ ደግሞ በማግስቱ የካቲት 24 ቀን 2005 ዓ.ም ከ3 ሰዓት ጀምሮ ነው::

የዝግጅቱ አስተባባሪዎች ለዝግጅት ክልችን እንደገለጹት ‹‹ አንድነት ፓርቲ በዓሉን የሚያከብረው የታሪክና የቋንቋ ምሁር በሆኑት በአቶ ሰለሞን ተሰማ በሚያቀርቡት የውይይት መነሻ ሐሳብ ሲሆን መኢአድ ደግሞ የአድዋን ገድል በሚያወሱና በሚዘክሩ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ይከበራል::

# 33ቱ ፓርቲዎች ዛሬ የመግባቢያ ስምምነት ይፈራረማሉ

በጥቅምት ወር በአዳማ የተሰባበሩት ፓርቲዎች ዛሬ በመኢአድ ጽህፈት ቤት የመግባቢያ ሰነድ እንደሚፈራረሙ የፓርቲዎቹ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶግርማ በቀለ ገለፁ። ከአራት ወር በላይ በውይይት የዳበረው የመግባቢያ ሰነድ ፓርቲዎቹ ከምርጫ ባሻገር አብረው የሚሰሩበትን መንገድ የጠረገ መሆኑን አቶግርማ አስረድተዋል። የፓርቲዎች ህብረት በየምክንያቱ መናዱ የነፃነት ናፋቂውን ህዝብ አንጀት ሲያሳርር ኖሯል። ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ፣ የስነዓቱን አምባገነናዊነትና ለኢትዮጵያ የማይበጅ አካሄድ በመቃወም የተመሰረቱ ስብስቦች በገዥው መደብ ሴራና በፓርቲዎች ቁርጠኝነት ማጣት ሲበታተን ታይቷል። በመሆኑም ጥቂት ያልሆኑ ፖለቲከኞች ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ወጥ ጠንካራ ፓርቲ መመስረት እንጂ የፓርቲዎች ስብስብ አይጠቅምም የሚል አቋም እስከመያዝ ደርሰዋል። ያም ቢሆን በፓርቲዎች ባለባቸው የገንዘብ፣ የሰው ኃይልና የተቋማዊ ብቃት ማነስ ሊሳካ አልቻለም። በኢትዮጵያ ፖለቲካ የጎላ ተፅእኖ ያመጣው የቀድሞው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ በመንግስት ሴራ ከተበተነ በኋላ የተመሰረተው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ አንድነት መድረክ ወደ ግንባር ደረጃ በማደግ ትግሉን አጠናክሮ ቀጥሏል። የመድረክ አባል ድርጅቶችን ጨምሮ በዓመቱ መጀመሪያ የተሰባሰቡት 33 ፓርቲዎች ጅማሮም ወደ ተሻለ ደረጃ በመድረስ ላይ መገኘቱ ለነፃነት ናፋቂው የኢትዮጵያ ህዝብ ተስፋ ሰጪ ሆኗል። ጥቅምት 15 ቀን 2005 ዓ.ም ምርጫ ቦርድ በአዳማ በተጠራው ስብሰባ ላይ የተቃውሞ ፊርማ በማሰባሰብ የተጀመረው የ33ቱ ፓርቲዎች ስብስብ ዛሬ በጋራ ያሰራናል በሚል ያረቀቁን የመግባቢያ ሰነድ በፊርማ ወደ ማፅደቅ ይሸጋገራል። ፓርቲዎቹ እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ የቻሉት በተደላደለ ጎዳና ግን አልነበረም። ይልቁንም የተለያዩ ፈታኝም ምዕራፎን አልፈዋል። በኢህአዴግ የሚመራው መንግስትና ገለልተኛ አለመሆኑን በተግባር ባረጋገጠው ምርጫ ቦርድ አሳፋሪ ተግባር ተፈፅሞባቸዋል። ጥያቄዎቻቸውን ካለመመለስ ጀምሮ የመሰብሰቢያ አዳራሾችን እንዳያገኙም ተደርገዋል። ይህ ድርጊት ከአምባገነንና ስርዓት የሚጠበቅ መሆኑን በመረዳት ጥያቄያቸውን አጠናክረው ለመቀጠል የወሰኑት 33ቱ ፓርቲዎች ከአዳማ እንደተመለሱ ያቋቋሙት ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ጠንካራ ስራ ሰርቷል። ፓርቲዎቹ ጥቅምት 29 ቀን 2005 ዓ.ም 18 ጥያቄዎችን ለምርጫ ቦርድ በማቅረብ የጋራ መግለጫ አውጥተው ነበር። ሆኖም ምርጫ ቦርድ ለጥያቄያቸው ተገቢን ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ፓርቲዎቹን ለመከፋፈል ያለመ ውሳኔ አስተላለፈ። ፓርቲዎቹ የቦርዱን ገለልተኛ አለመሆን በማስረጃ በማጋለጥ (የቦርዱ ሰብሳቢና ሌሎች ኃላፊዎች የገዢ ፓርቲ አባላት መሆናቸውን በማስረጃ ማጋለጣቸውን ልብ ይሏል) ጥያቄያቸውን ምርጫ ቦርድን ለሚዘውረው ኢህአዴግ ፅ/ቤት እና ለጠ/ሚ ቢሮ አቅርበዋል። ጨምረውም 18ቱን ጥያቄዎቻቸውን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ለአፈጉባኤ ፅ/ቤት በማስገባት በአቋማቸው ፀንተዋል። ገዥው ፓርቲና ምርጫ ቦርድ ጥያቄያቸውን ቸል በማለት የ2005 ዓ.ም የከተማ ምክር ቤትና የአካባቢ ምርጫ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ይካሄዳል በማለታቸው ከምርጫው ራሳቸውን ለመግለል በመወሰን ህዝባዊ ተቃውሞ ለማድረግ ያቀዱት ፓርቲዎቹ የመሰብሰቢያ አዳራሽ እንዳያገኙ በመንግስት ስውር ክልከላ ተደርጎባቸዋል። ሆኖም ተስፋ ባለመቁረጥ ከምርጫ ባሻገር በጋራ ለመታገል የሚያችስላቸውን ሰነድ በማዘጋጀት በዛሬው እለት በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ፅ/ቤት ይፈራረማሉ። ይህ የጋራ ትብብር ተጠናክሮ ግዙፍ የተቃዋሚ

# ለህሊና እስረኞች ሻማ ምሽት ጎፋ ማዞሪያ ሊደረግ ነው

ዘወትር ወር በገባ በሶስት ኢትዮጵያ ውስጥ ታስረው ለሚሰቃዩ የፖለቲካና የህሊና እስረኞች የሚደረገው የሻማ ምሽት ለመጀመሪያ ጊዜ ጎፋ ማዞሪያ ሊደረግ መሆኑን አስተባባሪ ኮሚቴው አስታወቀ። የዝግጅቱ አስተባባሪ ኮሚቴ ለዝግጅት ክፍላችን እንዳስታወቀው "የሻማ ምሽቱ ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ ሲከናወን የቆየው በአንድነት ፓርቲ ጽ/ቤት ነበር። የአንድነት ፓርቲ የወረዳ 20 እና ወረዳ 19 ጽ/ቤቶች በቅደም ተከተል በአቀረቡት ጥያቄ መሠረት ዝግጅቱን እንዲያዘጋጁ ተፈቅዶላቸዋል። በዚሁ መሠረት መጋቢት 03 ቀን 2005 ዓ.ም ከ10 ሰዓት ጀምሮ ጎፋ ማዞሪያ ዳውንታውንት ካፌ ፊት ለፊት በሚገኘው አንድነት ሆቴል ጀርባ "አንድ ታጋይ ቢታሠር ሺ ታጋይ ይተካል" በሚል መሪ ቃል ይከበራል ሲሉ አስተውቀዋል። በዝግጅቱ ላይ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ገኝተው ዝግጅቱን እንዲታደም አስተባባሪ ኮሚቴው ጥሪውን አቅርቧል።




